# ይድረስ ለኢትዮጵያ ልጆች!

ድንገት ሰው ሲያንኳኳ
ጠላት ይሁን ወዳጅ፣
ይከፈታል ደጅ፣
በሐገር ይዘት ግን እኛ የምንፈቅደው፤
ግቡም የምንለው፣
የኢትዮጵያን ልጆች ነው።
ሐገሪን ሊሸትን ሲያውጅብኝ ዛቻ
አልደራደርም፣ ለማስተናገድም
እራሴን አልገልም።
**መንደሪ ይሁንልኝ አገሪ ብለህ መሟገትህ፣**
**እጅጉን ገርሞኛል ወንድሜ**
**ይህን ግን ልጠይቅህ፤**
**አነስተኛን ጥቅም ምነዋ ተመኘህ?**
እንዲህ የወሰንኸው
ምኑ ቢታይህ ነው?
በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣
በሰሜን፣ በደቡብ፣ ኢትዮጵያ እያለች፣
እንዲህ ማቧረቅህ፣ መንደሪ አገሪ ነች፣
ያነ ካልሆነ ግን
በዱር እኖራለሁ ብለህ መሟገትህ፤
የኢትዮጵያ መበትንም ለኔ ይበቃኛል
ብለህ ማስታወቅህ።
ቻይና ሲበለጽግ ማንነቱን አውቆ
አሚሪካም ሲያቅድ ወደ ቪነስ ሊዘምት
በለንደን አዳራሽ ፉክራ አሰማህ
**ምኑ ነክቶህ ይሆን በአውሮጳ አስኳላ**
በፈረንጅ ቋንቋ ተምሪያለሁ ያልኸው
አቅም አጥተህ ይሆን ወይስ የለህም እውቅት፣
ይዘትህ እውን ነው
ስሚንቶ፣ ይቅርና ሚስማርም አታመርት፤
አሞትህን ፈሰሰ ስታስብ ቤት መሥራት?
ይሻለኛል ያልኸው በዱር አርጅቶ መሞት።
**እስኪ እንነጋገር በፈረንጆች ትምህርት**
**አንቱ የተባልኸው**
**መንደሪ ይሁን አገሪ ብለህ የተሟገትህ፣**
**እጅጉን ገርሞኛል ወንድሜ ልጠይቅህ፤**
**አነስተኛን ጥቅም ምነዋ አስመኘህ?**
አውሬው እኮ ብዙ ነው በጫካ ለመኖር
ይሻለኛል ያልኸው በዱር አርጅቶ መሞት፤
መግዛትህ አይቀርም ጠበንጃና ጥይት
ግራ ገብቶህ እንደሁ አዲስ ቤት መገንባት
አናጺውን ቀጥረህ  ይቻላል ማሰራት።

ምንህን ሰለበብህ የአውሮፓውያን ትምህርት፤
ለኢትዮጵያ መፈራረስ እንዲያ የምትመኝላት።
ፈረንጅ አስወድዶ ወገን የሚያስጠላህ
ምንስ መርዝ አጠጡህ
ያለህ ከፈረንጅ ቤት፣ መቸ ዱር ውሥጥ ነበርህ
ይህን ግን ላስታውቅህ፣
ቅዠት ውስጥ አትግባ፣ አትበርግግም በህልም፤
ዘላለማዊ ነች ኢትዮጵያ አትፈርስም።

© ለምለም ፀጋው ፣ November 3, 2016 አይሆንም ለማለት እንዲህ ላሰቡ ሁሉ

Source: Ethiomedia - https://www.youtube.com/watch?v=KnG6mhUZCC0